የነሐሴ 25 1997 ዓም ( ኦገስት31 2002 )

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## በራሱ ተማምኖ የቆየ ሕዝብ

## ማነኛውም ጥቃት አይበግረውም

"የትግል ቦታ በሆነችው በዚህች ዓለም ላይ፥ የሕዝቦች ታላቅነት የሚገመተው፥ የሚገጥማቸውን እንቅፋት አሸንፈው፥ ለመኖር በሚያሳዩት ብርታትና በሚፈጥሩት ዘዴ ነው::"

ከበደ ሚካኤል፥ ጃፓን እንደምን ሠለጠነች ገጽ 57

ኢትዮጵያ ሀገራችን በአለፉት አንድ መቶ ዓመታት ውስጥ ከአፈራቻቸው ታላላቅ ደራስያን መካከል ግንባር ቀደም ቦታ የነበራቸው ክቡር አቶ ከበደ ሚካኤል በድርሰቶቻቸው ሁሉ ሀገራቸው እንዴት መስልጠን እንዳለባት በሰፊው አመለክተው ነበር::: የወቅቱ መሪዎች አልተገነዘቡላቸውም:: በዘመኑ የነበሩት የሀገሪቱ መሪዎች ራዕይ ማጣት፥ አሁን ካለንበት ሁኔታ እንድንገኝ የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዳደረገ የሚያከራክር አይደለም:: ራዕይ የሌለው የሀገር መሪ፥ ከመከራው የሚያወጣው መሪ ያጣ ሕዝብ፥ የሁለት ዓለም ስደተኛ የሆነ ትውልድ፥ የቅርብ ጎረቤት- የሩቅ ዘመድ የተነፈጋት ሀገር ሕዝቦች ሆነን ቀርተናል:: ባዕዳን ወራሪዎችን ተቋቁሞ የቆየ ትውልድ የነበረባት ሀገር ብትሆንም፤ ዛሬ የወገን ጠላቶች ስለመጡባት፥ ከብሔራዊ ችግሩ ለመውጣት በሚያደርገው ትግል ተጨማሪ ዕንቅፋት ሆነውበታል:: ይህ የዛሬው ትውልድ እንደ ቀደምት አባቶቹና እናቶቹ ሁሉ፥ አሁን ካለበት ችግር መውጣት አለበት:: በግድም ይሁን በውድ! ሀገራችን የቀድሞ ታላቅነቷን ማስመለስ ፥ ማስከበርና ማረጋገጥ ይኖርባታል:: የራሱን ችግር እራሱ ማስወገድ ያልቻለ ትውልድ እየማቀቀ ይኖራታል እንጅ ማንም አይረዳውም:: እራሱን በራሱ መርዳት አለበት!

ይህንን በሚገባ የተረዳው የትላንቱ ትውልድ፥ በየጊዜው የገጠመውን ችግር እራሱ በገዛ እጁ ይፈታው ነበር እንጅ፥ እጁን አጣጥፎ የውጭ ርዳታ አይጠብቅም ነበር:: ሀገራዊ ነፃነቱንም ይሁን ብሔራዊ ኢኮኖሚውን በውጭ ርዳታና ትብብር ብቻ ሊቀይስና ሊገነባ የሚመኝ ሀገርና ሕዝብ በዘለቄታ መልኩ ከችግሩ ይወጣል ተብሎ የሚጠበቅ ሊሆን አይችልም:: የዛሬውን አይሁንና፥ ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ሀገራችን፥ ለዘመናት ነፃነቷን አስከብራ የቆየችው፥ በራሱ የሚተማመን ዜጋ ስለነበራት ብቻ ነው:: የጥንት ታሪካችንን ዜና መዋዕል የመዘርዘሩን ተግባር ለታሪክ ፀሀፊዎች እንተወውና፥ በአለፉት አንድ መቶ ዓመታት ታሪካችን ላይ እንኳ ብናተኩር፥ በራስ መተማንን አስመልክቶ ጠቃሚ ትምህርት ልናገኝ እንችላለን:: በአደዋ ጦርነት አኩሪ ድልን የተጎናፀፈው ትውልድ፥ በዘመኑ ኃይል የነበረችውን የኢጣሊያንን

ወረራ የደመሰሰው በራሱ በግሉ እንጅ፥ የውጭ ርዳታ አግኝቶ አልነበረም። ዕርግጥ የሩሲያ ቀይ መስቀል ማኅበር የሕክምና ርዳታ ትብብር አሳይቷል። ለዚህም ኢትዮጵያ ለሩሲያኖች ባለውለታ ነበረች። ከአርባ ዓመታት በኋላ ደግሞ የአድዋን ቂሟን ለመወጣት እንደገና በዘመናዊ የጦር መሳሪያ ተደራጅታ በመምጣት በ1928 ዓም ኢጣሊያ በማይጨው ጦርነት በለስ ቢቀናትም፥ የኢትዮጵያ አርበኞች ከአምስት ዓመታት መሪር ተጋድሎ በኋላ ጣሊያንን አባርረው ነፃነትን ለማስመለስ በቅተዋል። በአምስቱ ዓመታት ጦርነት ይህ ነው የሚባል የማነኛውን ትልቅ የውጭ ርዳታ አላገኙም። አብዛኛው ዓለም፥ ለኢትዮጵያ በኢጣሊያ መወረርና ሕዝቧም በመርዝ ጋዝ መጨፍጨፍ ምንም ደንታ አልነበረውም። እንዲያውም ኢትዮጵያ ራሷን ለመከላከል የሚያስችላትን ህጋዊ የጦር መሳሪያ እንዳታገኝ ተፈርዶባት ነበር። በዘመኑ የዓለም ማኅበር እየተባለ ይጠራ የነበረው የመንግሥታት ጉባዔ አባል የነበረች ብትሆንም፥ ሀገራችን በዲፕሎማሲውም ይሁን በቆሳቁስ፥ ርዳታ እንዳታገኝ ከልክሏት ነበር። በዚህ ሸንጎ፥ ተወርሪያለሁና አስጥሉኝ ብላ ብታመለከትም ጩኸቷ ሰሚ ሳያገኝ ቀርቷል። በኋላ ግን፥የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ዕሳት እነርሱን ሲለበልባቸው፥ ለራሳቸው አጋር ትሆነናለች ብለው በማሰብ የኢትዮጵያን አርበኞች ትብብር ለመፈለግ ተገደዋል። ምን ጊዜም ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ የውጭን ርዳታ ተማምኖ አያውቅም።

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዘረኞች አምባገነን አገዛዝ ለመውጣት የሞት ሽረት ትግል በማድረግ ላይ ይገኛል። በአለፉት አስራ አራት ዓመታት ውስጥ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ አስደሳች መልኩ፥በዓለም ዙሪያ የተሰራጨው ኢትዮጵያዊ ዜጋ በከፍተኛ ደረጃ ተባብሮ ሀገሩን ነፃ ለማውጣት በመታገል ላይ ነው። የሀገር ቤቱና የውጭው ትግል በሚያበረታታ ደረጃ ተቀናጅቶ በመካሄድ ላይ ይገኛል። ይህን ለማኮላሸት፥ መለስና ግብረ-አበሮቹ በመራወጥ ላይ ናቸው። የሀገር ቤቱን የሕዝብ ትግል ለማኮላሸት ከሚያደርጉት አጉል መፍጨርጨር ሌላ፥ በውጭ ያለውን ኢትዮጵያውያን/ት የተባበበረ ትግልና ተቃውሞ ለመከፋፈል መለስ ዜናዊ አዲስ ዕቅድ አውጥቶ ወኪሎቹን በማንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። አንድ ሕዝብ በራስ የመተማመኑን ጉለበትና ችሎታ ሊያገኝ ከፈለገ፥ በሁለንተናዊ አቅጠጫ እራሱን አስታጥቆ ሊደራጅ የግድ ይሆንበታል። የሁሉም ቆም ነገር መሠረት ግን ተባብሮ በኅብረት የመቆሙ ጉዳይ መተኪያ አይገኝለትም። የተከፋፈለች መንግሥት እንደማትቆም ሁሉ፥ ያለተባበረ ሕዝብም ሀገሩ ተከፋፍላ እንድትንኮታኮት ምክንያት ለመሆን ይችላል። ይህ ሊሆን አይገባውም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገሩን ከነመለስ ዜናዊ አጥፊ ቡድን ነፃ ማውጣት ያለው አማራጭ በመሠረቱ አንድ ብቻ ነው ማለት ይቻላል። በራሱ ኅብረትና ትብብር፥ ዕምነትና ጉልበት፥ ዕውቀትና ኃይል መተማመን!

በአለፋው ሳምንት የአውሮፓ ኅብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን የግንቦቱን ምርጫ አስመልክቶ ሰፊና ዝርዝር ዘገባውን ይፋ አደረጓል። ምርጫው የዓለም አቀፍን መስፈርት ያላሟላና የተፃረረ፥ የተጭበረበረና የኢትዮጵያንም ሕዝብ

የዴሞክራሲ ተስፋና ምኞት ያከላሸ እንደነበር በግልፅ መስክሯል። በዚህ ዘገባ በመመርኮዝም አያሌ ዓለም አቀፍ ተቋማና በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲ ሥርዓት መስፈን ፍላጎታቸውን ያሳዩ የኅብረተስብ ክፍሎች ሀዘናቸውን አሰምተዋል። ተቃውሟቸውንም አስመዝግበዋል። ይህ ሁኔታ መቸም አውንታዊ እንደሆነ የኢትዮጵያ ሕዝበ ይገነዘባል። ሀገራችን የዓለም ኅብረተስብ አባል በመሆኗም፥ የዓለም አቀፍን ትብብር፥ ድጋፍና አውንታዊ ግንዛቤን ትፈለጋለች። ይህ እንዳለ ቢሆንም፥ የኢትዮጵያን ዘላቂ ጥቅምና ዕድል የመወሰኑና የመጠበቁ ተግባር የእኛው የበለቤቶቹ የኢትዮጵያውያን ብቻ መሆኑን ለአንዳፍታም ቢሆን ሊዘነጋ አይገባም።

ይህ በምዕራብውያንም ሆነ ምሥራቃውያን የመተማመኑ ባኅርይና አዝማሚያ መቅረት አለበት። የኢትዮጵያን አንድነትና ኅልውና እንዲናጋ ያደረጉትን ሀገሮች እንደገና መለማመጥና መተማመን የከንቱ ከንቱነት ነው የሚመስለን። ሰባ ሚሊዮን ሕዝብ ተባብሮ የሀገሩን ችግር ማስወገድ ካልቻለ፥ ማንም ባዕዳን መፍትሄ ያመጣልናል ተብሎ አይታሰብም። ብዙኃን የኢትዮጵያ ፖሊቲካ ታዛቢዎችና ተከታታዮች፥ የሰሞኑ የአውሮፓ ኅብረት ዘገባ፥ ለተቃዋሚው ክፍል የኅብረት ትግል ከፍተኛና ሰፊ ዕድል እንደከፈተለት ቆጥረውታል። ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም፥ ሁሉም የፖለቲካ ተቃዋሚ ክፍሎች ኅብረታቸውን በማጠንከር የጋራ የትግል ዕቅድ አውጥተው ወያኔን ከሥልጣን ለማውረድ ቢንቀሳቀሱ ባጭር ጊዜ ውስጥ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚችሉ ጥርጥር አይኖረውም። የወቅቱን የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ በሚገባ ለተገነዘበ ታዛቢ፥ ለተቃዋሚው ጎራ ሁሉም ነገር ተሳክቶ እንደቀረበለት ሊረዳ ይችላል። <u>ሦስት</u> መሠረታዊና ወሳኝ ሁኔታዎች ቁልጭ ብለው መጥተውለታል። እነርሱም፦

ሀ) የወያኔን አገዛዝ ተቃውሞ አልገዛም ባይነቱን በመስዋዕት እያስመሰከረ የሚታገል ሕዝብ መጥቷል። ይህ ኃይል ደግሞ በሚገባ ከተጠቀሙበት ወሳኝና የማይበገር ኃይል ነው።

ለ) የዓለም አቀፍ ኅብረተስብ በልዩ ልዩ መንገዶች የወያኔን አገዛዝ እየተቃወመና የነበረውንም ድጋፍ እየነሳው ይገኛል። ይህንን የዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲ ምቹነት በሚገባ መጠቀም የተቃዋሚው ጎራ ኃላፊነትና ብልኀነት ይመስለናል። ምቹ አጋጣሚን ተጠቅሞ፥ ውጤት ማስመዝገብ፥አንገብጋቢና ወሳኝ ነው።

ሐ) መለስ ዜናዊ ወደደም ጠላ፥ ዛሬ የወያኔ አገዛዝ ጃርት የበላው ዱባ ሆኗል። ባብዛኛው፥ የትግራይን ሕዝብም ጭምር ድጋፍና ትብብር አጥቷል። የለመደውን የክፍፍል ዘዴ ለመጠቀም ሞክሮ ሳይሳካለት ቀርቷል። የትግራይ ምሁራንና ዴሞክራሲያዊ ኃይላት ከቀሪው የኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጋር ስለ ጋራ ሀገራቸው ጉዳይ እየመከሩ-እየዘከሩ ነው። ይህም የመለስ ዜናዊን ዕኩይ ኅሊና እየረበሸው ይገኛል። እየተቀበዘበዘም ነው።

ይህን አጋጣሚ በሚገባ ገምግሞ አዲስ የትግል ዕቅድና ስልት በመቀየስ ሕዝቡን አስተባብሮ፥ ወያኔን በማስወገድ የዴሞክራሲ ሥርዓት ማምጣት ቀነ ቀጠሮ የሚሰጠው ጉዳይ ሊሆን ከቶ አይገባውም፡፡ የተቃውሞ ሰለፍ ማዘጋጀትና መግለጫ ማውጣት የትግል ዘርፎች መሆናቸው ባይካድም፤ ሕዝብን ለሰላማዊ አመፅ አዘጋጅቶ ይህን የተጠላ ሥርዓት ማንበርከክ ግን የትግሉ የመጨረሻው ግብ ሊሆን ይገባል፡፡ ዛሬ፥ ኢትዮጵያ ሀገራችን በታሪኳ ገጥመዋት የማያውቁ ውስብስብ ችግሮች አሉባት፡፡ የአንድ ሀገር ሕዝብ ታላቅነቱን የሚያስመሰክረው፥ በታሪኩ የሚገጠመውን ችግር አስወግዶ በአሸናፊነት ሲወጣ ለመሆኑ፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማስረዳት፥ ማንም የሞራል ሥልጣን አለው ብለን አናምንም፡፡ ምክንያቱም፥ በታሪኩ ደጋግሞ በተግባር የገለፀው በመሆኑ ነው፡፡ በራሳችን ተማምነን ችግሮቻችንን አስወገደን ማንነታችንን ለማስረገጥ ተባብረን እንነሳ! የወቅቱ ተልዕኮአችን ሊወደቅ የደረሰውን የመለስ አገዛዝ ጊዜ ሳንሰጥ ወደ መቃብሩ መክተት ነው፡፡

---------------